ሰነገ ሳያስተርፉ ያገኙትን ሁሉ በልተው እንደ
ሚጨርሱ እንደተራቡ የማታ ተኲላዎች
ናቸው። 4 ነቢያትዋ በትዕቢት የተወጠሩና
በተንኰል የተሞሉ ናቸው፤ ካህናትዋ የተቀደሰ
ውን ያረክሳሉ፤ የእግዚአብሔርንም ሕግ ለራሳ
ቸው እንደሚስማማ አጣምመው ይተረጕማሉ፤
5 እውነተኛ የሆነ እግዚአብሔር ግን አሁንም
በውስጥዋ አለ፤ እርሱ ስሕተትን ፈጽሞ አያደር
ግም፤ እርሱ በየማለዳው እውነተኛ ፍርድን
ለሕዝቡ ይሰጣል፤ በየዕለቱም ይህን ከማድረግ
አይቈጠብም፤ ይህም ሁሉ ሆኖ በዚያ የሚኖ
ረው ዐመፀኛ ሕዝብ በደልን ያለ ሐፍረት ይፈ
ጽማል።

6 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ "የአሕዛብን
መንግሥታት አጠፋሁ፤ ምሽጎቻቸውን አፈራረ
ስሁ፤ ከተሞቻቸውንም ደመሰስሁ፤ ከተሞቻ
ቸው ማንም የማይኖርባቸው ወና ስለሆኑ በመን
ገዶቻቸው የሚተላለፍ ሰው የለም። 7 እኔም
ይህን ሁሉ በማድረጌ 'ሕዝቤ ያከብረኛል፤ ተግ
ሣጼንም ይቀበላል፤ ያደረግሁለትንም ውለታ
ሁሉ አይረሳም' ብዬ ነበር፤ ሕዝቡ ግን እየባሰ
በት ሄደ፤ በክፉ ሥራውም ረከሰ።"

8 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ "ጥቂት
ታገሡ፤ በእነርሱ ላይ የምፈርድበት ጊዜ ይመ
ጣል፤ አሕዛብንና መንግሥታትን በአንድነት
እሰበስባለሁ፤ የቍጣዬንም እሳት በእነርሱ ላይ
አፈስሳለሁ፤ በቍጣዬም እሳት መላዋ ምድር
ትቃጠላለች።

9 "በዚያን ጊዜ የሕዝቦችን አሳብ እለውጣ
ለሁ፤ ይኸውም ወደ ሐሰተኞች አማልክት ሳይ
ሆን ወደ እኔ በንጹሕ ኅሊና እንዲጸልዩ አደርጋ
ለሁ፤ ሁሉም በአንድነት እኔን ያገለግላሉ።
10 በስደት ተበታትነው የሚኖሩት ወገኖቼ
በሩቅ ካለችው ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ መባ
ይዘውልኝ ይመጣሉ። 11 በእኔ ላይ ስለፈጸማች
ሁት በደል በዚያን ጊዜ አታፍሩበትም፤ ምክን
ያቱም ትዕቢተኞችንና ትምክሕተኞችን ከመካ
ከላችሁ አስወግዳለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ በተቀ
ደሰው ተራራዬ በእኔ ላይ አታምፁብኝም።
12 ከመካከላችሁ ራሳቸውን ዝቅ ያደረጉ ትሑ
ታን ሕዝቦችን አስቀራለሁ፤ እነርሱም በእኔ
የሚታመኑና የእኔንም ዕርዳታ የሚሹ ይሆ
ናሉ። 13 ከምርኮ የተረፉት የእስራኤል ሕዝብ
በማንም ላይ ክፉ ነገር አያደርጉም፤ ሐሰት
አይናገሩም፤ በእንደበታቸውም አያታልሉም፤
ስለዚህም በልጽገው በሰላም ይኖራሉ፤ የሚያስ
ፈራቸውም የለም።"

*የደስታ መዝሙር*

14 የጽዮን ልጅ ሆይ! ዘምሪ!
የእስራኤል ሕዝብ ሆይ!
ዘምሩ! እልልም በሉ!
የኢየሩሳሌምም ልጅ ሆይ!
በሙሉ ልብሽ ደስ ይበልሽ፤
ሐሴትም አድርጊ።
15 እግዚአብሔር በእናንተ ላይ
ያስተላለፈውን
የቅጣት ፍርድ አንሥቶላችኋል፤
ጠላቶቻችሁንም አስወግዶላችኋል፤
የእስራኤል ንጉሥ የሆነው እግዚአብሔር
በመካከላችሁ ስለሆነ፥
ከእንግዲህ ወዲህ የሚያስፈራችሁ ነገር
የለም።
16 በዚያን ጊዜ ስለ ኢየሩሳሌም እንደዚህ
ይባልላታል፤
"የጽዮን ከተማ ሆይ! አትፍሪ!
ክንዶችሽም አይዛሉ፤
17-18 እግዚአብሔር አምላክሽ ከአንቺ ጋር
ነው፤
በኀይሉም ድልን ያጐናጽፍሻል፤
እግዚአብሔር በአንቺ ደስ ይለዋል፤
በፍቅሩም ሕይወትሽን በማደስ
ያሳርፍሻል፤
ሕዝቦች በበዓል ቀን እንደሚያደርጉት፥
ስለ አንቺ ያለውን ደስታ በመዝሙር
ይገልጣል።"
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦
"ከእንግዲህ ወዲህ ጥፋት
እንዳይደርስብሽ አደርጋለሁ፤
ሐፍረትሽንም አስወግዳለሁ፤
19 ሲያስጨንቁሽ የኖሩትን ሁሉ በዚያን
ጊዜ እቀጣለሁ፤
ያነከሱትን ሁሉ እታደጋለሁ፤
የተሰደዱትንም መልሼ እሰበስባቸዋለሁ፤
ሐፍረታቸውንም ወደ ክብር
እለውጣለሁ፤
ስለዚህም በምድር ላይ የሚኖሩ
ሕዝቦች ሁሉ ያከብሩአቸዋል።
20 በስደት የተበታተኑትን ሕዝብሽን በዚያን
ጊዜ እመልሳቸዋለሁ፤
በዓለም ሕዝብ መካከል
የታወቃችሁ ዝነኞች አደርጋችኋለሁ፤
እንደገናም አበለጽጋችኋለሁ።"
ይህንንም የተናገረ እግዚአብሔር ነው።

---

3፥13 ፦ ራእ. 14፥5።

# ትንቢተ ዘካርያስ

## መግቢያ

ትንቢተ ዘካርያስ በሁለት ክፍሎች የተመደበ ነው ፤

1. ክፍ. 1-8 ከአምስት መቶ ሃያ እስከ አምስት መቶ ዐሥራ ስምንት ዓመተ ዓለም ባሉት ዓመታት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ነቢዩ ዘካርያስ የተናገራቸውን የትንቢት ቃላት የያዘ ክፍል ነው ፤ እነዚህም የትንቢት ቃላት በራእይ መልክ የቀረቡ ሲሆን ፣ ስለ ኢየሩሳሌም መታደስ ፣ ስለ ቤተ መቅደሱ እንደገና መሠራት ፣ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ መንጻትና ወደፊት ስለሚመጣው የመሲሑ ዘመን የሚናገሩ ናቸው ።
2. ክፍ. 9-14 ያለው ክፍል ዘግየት ብለው የተነገሩትን የትንቢት ቃላት የያዘ ነው ፤ እነዚህም የትንቢት ቃላት የሚናገሩት ወደፊት ስለሚመጣው መሲሕና ስለመጨረሻው ፍርድ ነው ።

---

## ምዕራፍ 1

### እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲመለሱ ሕዝቡን ጠራ

1 ዳርዮስ የፋርስ ንጉሥ በሆነ በሁለተኛው
ዓመት ፣ በስምንተኛው ወር እግዚአብሔር
በዒዶ የልጅ ልጅ በቤሬክያ ልጅ በነቢዩ በዘ
ካርያስ አማካይነት የተናገረው የትንቢት ቃል
ይህ ነው ፤ 2 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለዘካ
ርያስን ለሕዝቡ እንዲህ ብለህ ተናገር አለው ፣
“እኔ እግዚአብሔር በቀድሞ አባቶቻችሁ ላይ
እጅግ ተቈጥቼ ነበር ፤ 3 አሁን ግን እናንተን
የምላችሁ ይህ ነው ፦ ወደ እኔ ተመለሱ ፤
እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ፤ 4 የቀድሞ
አባቶቻችሁን ዱካ አትከተሉ ፤ እነርሱን የቀ
ድሞ ነቢያት ‘ከክፉ መንገዳችሁና ከክፉ
ሥራችሁ ተመለሱ’ ብለው እስጠንቅቀዋቸው
ነበር ፤ አባቶቻችሁ ግን ቃሌን አላደመጡም ፤
ትእዛዜንም አልጠበቁም ። 5 የቀድሞ አባቶቻች
ሁም ሆኑ በእነርሱ ዘመን የነበሩት ነቢያት
እነሆ አሁን በሕይወት የሉም ። 6 አገልጋዮቼ
በሆኑት በነቢያት አማካይነት ለቀድሞ አባቶቻ
ችሁ ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ ሰጥቻቸው
ነበር ፤ እነርሱ ግን ችላ ከማለታቸው የተነሣ
አሠቃቂ መከራ ደረሰባቸው ፤ ከዚያም በኋላ
ተጸጽተው ‘የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እንደ አካሄዳችንና እንደ ሥራችን ተገቢ
ቅጣት ወስኖ እንደሰጠን ተገንዝበናል’
አሉ ።”

### ነቢዩ ዘካርያስ ስለ ፈረሶች ያየው ራእይ

7 ዳርዮስ በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ፣ ሸባጥ
የተባለው ዐሥራ አንደኛው ወር በገባ በሃያ አራ
ተኛው ቀን ፣ እግዚአብሔር በሌሊት ራእይ የነ
ገረኝ ቃል ይህ ነው ፤ 8 የእግዚአብሔር መልአክ
በቀይ ፈረስ ላይ ተቀምጦ አየሁ ፤ እርሱም በሸ
ለቆው ውስጥ ባሉ በባርሰነት ዛፎች መካከል
ቆመ ፤ በስተኋላውም ቀይ ፣ ሐመርና አምባላይ
ፈረሶች ይከተሉት ነበር ። 9 እኔም “ጌታዬ
ሆይ! እነዚህ ፈረሶች የምን ምሳሌ ናቸው?”
ብዬ ጠየቅሁት ።

እርሱም “የእነዚህ ፈረሶች ምሳሌነት ምን
እንደሆነ አሳይሃለሁ ። 10 እነርሱ ምድርን እንዲ
ፈትሹ እግዚአብሔር የላካቸው ናቸው”
አለኝ ። 11 ፈረሶቹም “በምድር ሁሉ ላይ ተመ
ላልሰን አይተናል ፤ እነሆ ዓለም በሙሉ በዕረፍ
ትና በሰላም ይገኛል” ብለው ለመልአኩ ነገ
ሩት ።

12 መልአኩም “የሠራዊት ጌታ እግዚአብ
ሔር ሆይ! ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች
ሁሉ ከተቈጣህ እነሆ ሰባ ዓመታት አለፉ ፤
ምሕረት እስክታደርግላቸው ድረስ ከእንግዲህ
ወዲህ ምን ያህል ጊዜ ይቀራል?” ሲል ጠየቀ ።
13 እግዚአብሔርም መልአኩን ደስ በሚያሰ
ኝና በሚያጽናና ቃል ተናገረው ፤ 14 ስለዚህም
መልአኩ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚለ
ውን ቃል እንዲህ ብለህ ዐውጅ አለኝ ፣ “እኔ
ለተቀደሰችው ከተማዬ ለኢየሩሳሌም ታላቅ

---

1፥1 ፦ ዕዝ. 4፥24-5፥1 ፤ 6፥14 ። 1፥8 ፦ ራእ. 6፥2-8 ።

መቅደሱ መፍረስ ማዘናችንን እንቀጥልን?”
ብለው እንዲጠይቁ ነበር።
4 ከዚህም በኋላ ወደ እኔ የመጣው የእግዚአ
ብሔር ቃል ይህ ነው፤ 5 “ባለፉት ሰባ ዓመ
ታት በአምስተኛውና በሰባተኛው ወር የጾሙ
ትና ያዘኑት እኔን በማክበር እንዳልሆነ ለሕዝ
ቡና ለካህናቱ ንገራቸው፤ 6 ይበሉና ይጠጡ የነ
በሩትም ለራሳቸው ብቻ ነበር።”
7 ኢየሩሳሌም በልጽጋና በሕዝብ ተሞልታ
በነበረችበት ጊዜ፥ በከተማይቱ ዙሪያ ባሉ መን
ደሮች ብቻ ሳይሆን በደቡብ ክፍልና በምዕራብ
ኰረብቶች ግርጌ ብዙ ሕዝብ በሚኖሩበት ዘመን
እግዚአብሔር በቀድሞ ነቢያቱ አማካይነት የተ
ናገረውም ይህንኑ ቃል ነበር።

### አለመታዘዝ የስደት ምክንያት ሆነ

8 እግዚአብሔር ዘካርያስን እንዲህ ሲል ተና
ገረው፤ 9 “እኔ የሠራዊት ጌታ ለሕዝቤ የሰጠ
ሁት ትእዛዝ ይህ ነበር፤ ይኸውም ‘በትክክል
ፍረዱ፤ እርስ በርሳችሁም እንዳችሁ ለሌላው
ምሕረትና ርኅራኄን አድርጉ፤ 10 በመካከላችሁ
የሚኖሩትን ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች፥
አባትና እናት የሌላቸውን ድኻ አደጎች፥ መጻ
ተኞችንና ችግረኞችን አትጨቍኑ፤ እርስ በርሳ
ችሁ እንዳችሁ ሌላውን ለመጒዳት አታስቡ።’
11 “ሕዝቤ ግን በእልኸኛነት አናዳምጥም
ብለው እምቢተኝነታቸውን አጸኑ፤ 12 ልባቸው
ንም እንደ አለት ድንጋይ አጠነከሩ፤ ጥንት በነ
በሩበት ነቢያት አማካይነት በመንፈሴ የሰጠኋቸ
ውን ትእዛዝ ሁሉ በእልኸኛነት ‘አናዳምጥም’
በማለታቸውም ምክንያት፥ እኔ በእነርሱ ላይ
እጅግ ተቈጣሁ። 13 እኔ ስናገር ‘አናዳምጥም’
ስላሉ፥ እነርሱም ወደ እኔ በጸለዩ ጊዜ መልስ
አልሰጠኋቸውም። 14 እንደ ዐውሎ ነፋስ ጠራ
ርጌ በመውሰድም በማያውቁት ባዕድ አገር እን
ዲኖሩ አደረግሁአቸው፤ ይህችም መልካም
ምድር ማንም የማይኖርባት ባድማ ሆና
ቀረች።”

## ምዕራፍ 8

### ኢየሩሳሌምን ወደ ቀድሞ ሁኔታዋ ለመመለስ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ

1 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘካርያስን
እንዲህ ሲል ተናገረው፤ 2 “ለሕዝብዋ ስላለኝ
ፍቅር ኢየሩሳሌምን መርዳት እፈልጋለሁ፤ በጠ
ላቶችዋ ላይ እንድቈጣ ያደረገኝም ይኸው ስለ
እርስዋ ያለኝ ፍቅር ነው። 3 እኔ እንድኖርባት
ወደ ተቀደሰችው ከተማዬ ወደ ኢየሩሳሌም
እመለሳለሁ፤ የታመነች ከተማ በመሆን ትታወ
ቃለች፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚኖር
በት ተራራ፥ የተቀደሰ ተራራ ተብሎ ይጠ
ራል፤ 4 በትር ተመርኲዘው እስኪሄዱ ድረስ
ያረጁ ወንዶችና ሴቶች እንደገና በከተማይቱ
አደባባዮች ይቀመጣሉ። 5 አደባባዮችዋም ሁሉ
በሚጫወቱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደገና
የተሞሉ ይሆናሉ።
6 “ይህ፥ አሁን በምርኮ ከመወሰድ ለተረ
ፉት ሰዎች የማይቻል ነገር መስሎ ይታያቸው
ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ለእኔ የማይቻል ነገር
አይደለም። 7 እኔ ሕዝቤን በስደት ከሚኖሩበት
አገር አታደጋቸዋለሁ፤ ከምሥራቅና ከምዕ
ራብ፥ 8 መልሼ በማምጣት በኢየሩሳሌም እንዲ
ኖሩ አደርጋቸዋለሁ፤ እነርሱ ሕዝቤ ይሆናሉ፤
እኔም አምላካቸው እሆናለሁ፤ በቅንነትና በእ
ውነት እመራቸዋለሁ።
9 “ቤተ መቅደሱ እንደገና እንዲሠራ መሠ
ረቱ በተጣለ ጊዜ ነቢያት የተናገሩትን አሁን
የምትሰሙ ሁሉ አይዞአችሁ በርቱ! 10 ከዚያን
ጊዜ በፊት በሰዎች መካከል ጠብና ክርክር እን
ዲበዛ አድርጌ ነበር፤ ከጠላት ለመዳን ካለመ
ቻሉ የተነሣ በሰላም ለመኖር የሚችል አልነበ
ረም፤ ሰዎችን በገንዘብ መቅጠር፥ እንስሳትንም
መከራየት ከቶ አይቻልም ነበር። 11 አሁን ግን
ከዚህ ሕዝብ የተረፉትን እንደ ቀድሞው ጊዜ
አላደርግባቸውም። 12 እህላቸውን በሰላም ይዘ
ራሉ፤ የወይን ተክሎቻቸው ፍሬያማ ይሆናሉ፤
ብዙ ዝናም ስለሚኖር ምድር ብዙ ሰብል ታስገ
ኛለች፤ ከሕዝቤ ለተረፉት ይህን ሁሉ በረከት
እሰጣለሁ። 13 እናንተ የይሁዳና የእስራኤል
ሕዝቦች ሆይ! ከዚህ በፊት የምድር አሕዛብ
‘በእነዚህ ሕዝቦች ላይ የደረሰ መርገም ይድረስ
ባችሁ’ እየተባባሉ መዘባበቻ አድርገዋችሁ
ነበር፤ አሁን ግን እኔ አድናችኋለሁ፤ እንደገ
ናም ‘ለነዚህ ሕዝቦች የተሰጠ በረከት ለእናን
ተም ይድረሳችሁ’ መባባል ይጀምራሉ። ስለዚ
ህም አይዞአችሁ! በርቱ! አትፍሩ።”
14 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ “የቀድሞ አባቶቻችሁ ባስቈጡኝ ጊዜ
ባቀድሁት መሠረት ጥፋት እንዲመጣባቸው
አደረግሁ እንጂ ውሳኔን አልለወጥሁም።
15 አሁን ግን የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ሕዝቦች
ለመባረክ ቍርጥ ውሳኔ አድርጌአለሁ፤ ስለዚህ
አይዞአችሁ አትፍሩ! 16 እናንተ ልታደርጉት
የሚገባ ነገር ይህ ነው፤- እርስ በርሳችሁ እው
ነት ተነጋገሩ፤ በፍርድ ሸንጎዎቻችሁ ሰላም
የሚገኝበትን እውነተኛ ፍርድ ስጡ። 17 እርስ
በርሳችሁ ለመጒዳዳት እንዱ በሌላው ላይ
ተንኰል አያስብ፤ ምላችሁ በሐሰት አትመስ
ክሩ፤ እኔ ሐሰትንና ግፍን ሁሉ የምጠላ አም
ላክ ነኝ።”
18 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘካርያስን
እንደገና እንዲህ አለው፤ 19 “በአራተኛው፥

8፥16 ኤፌ. 4፥25።

## ምዕራፍ 4

### የጌታ ቀን ቀርቦአል

1 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤ "ትዕቢተኞችና ክፉ አድራጊዎች እንደ
ገለባ በእሳት የሚጋዩበት ቀን ቀርቦአል፤ በዚ
ያን ጊዜ ከእነርሱ ማንም ሳይተርፍ ተቃጥለው
ይጠፋሉ። 2 ለምትታዘዙኝ ለእናንተ ግን የጽ
ድቅ ፀሐይ ይወጣላችኋል፤ ፈውስንም ይሰ
ጣችኋል፤ ነፃ ወጥታችሁም ከማለሪያው ተለቆ
በደስታ እንደሚብዋርቅ እንቦሳ ትሆናላችሁ።
3 እኔ በምሠራበት በዚያ ቀን ዐመፀኞችን ሁሉ
ታሸንፋላችሁ፤ በእግራችሁም ጫማ ሥር እንደ
ትቢያ ይሆናሉ።

4 "የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እንዲፈጽሙት
በሲና ተራራ ላይ ለአገልጋዬ ለሙሴ የሰጠ
ሁትን የሕግና የትእዛዝ ትምህርት አስታ
ውሱ።

5 "ነገር ግን ታላቅና አስፈሪ የሆነው የጌታ
ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩን ኤልያስን ወደ
እናንተ እልክላችኋለሁ። 6 እርሱም መጥቼ
ምድራችሁን እንዳላጠፋ ተለያይተው የነበሩትን
አባቶችና ልጆች ልብ ለልብ እንዲቀራረቡ ያደ
ርጋቸዋል።"

---

4፥5 ፦ ማቴ. 11፥14፤ 17፥10-13፤ ማር. 9፥11-13፤ ሉቃ. 1፥17፤ ዮሐ. 1፥21።